# የአማራ ምሁራን ጉበኤ መግለጫና ታሪካዊ ስህተቶች

## ( መይሳው አማራ)

ለአንድ ህዝብ/ሀገር እድገት የምሁራን አስተዋፆ ከዚህ እስከዚህ ተብሎ የሚለካ/የሚተመን አይደለም። አዳዲስ ቴክኖሎጆችን በመፍጠርና ልማትን በማሳለጥ፣ የህብረተሰቡን አስተሳሰብ ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ በማድረግ፣ ዲሞክራሲያዊ ስርአት እንዲፈጠር አቅጣጫ በመጠቆም፣ የስራ ዕድል የሚፈጠርበትን የአሰራር ስልት በመንደፍ፣ የተሻለ ሥርዓት ትምህርት በመቅረጽ ለሀገር አለኝታ የሆነ ወጣት በማፍራት ምሁራን የማይተካ ሚና አላቸው።ሀገራችን በድህነት አሮንቃ የምትገኝበት አንደኛው ምክንያት መንግስት ጸረ-ምሁራን ሆኖ በመቆየቱ ነው። የሰሞኑን የጠቅላይ ሚ/ር አቢይ አህመድ ጸረ-ምሁራን መግለጫ፣ የ1984ዓ.ም አቶ መለስ ዜናዊ 42 የአዲስ አበባ ምሁራንን ያባረረበትን ጸረ-ምሁራን እርምጃ እንደምሳሌ መጥቀስ እንችላለን።

አለመታደል ሆኖ ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰአት እንደ ሀገር ያላትን ምሁራን አሰባስባ መጠቀም የምትችልበት ሁኔታ ላይ አይደለችም። በሀገሪቱ ውስጥ ያለው የብሄር ፖለቲካ ምሁራንን በዘር ከፋፍሎ እርስ በርስ የሻኩራ እንዲተያዩ በማድረግ የነበራቸውን አንድትና የፈጠራ ነፃነት በመንጠቅ የፖለቲካ ጥገኛ ካደረጋቸው ሰነባብቷል።

በዚህች የብሄር ፖለቲካ በነገሰባት ሀገር የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ለመረዳት እጅግ ረጅም ጊዜ የወሰደበት የአማራ ምሁራን ነው። ላለፉት ሩብ አመታት የትግሬና የኦሮሞ ምሁራን ከፖለቲከኞች ጋር በማበር/በማሴር የራሳቸውን ህዝብ በሚጠቅም ስራ ውስጥ ተጠምደው ከመቆየታቸው በላይ የአማራውን ታሪክ በማዛበትና የአማራን ስነ -ልቦና በማዳከም ላይ መቆየታቸው የሚታወቅ ሐቅ ነው።

በተቃራኒው የአማራ ምሁራን በትግሬና በኦርሞ ምሁራን፤ በህወሓትና ኦነግ ሲፈበረክ የኖረውን ጸረ-አማራ ትርክት በመመከ ህዝባቸውን ማንቃት ሲገባቸው ራሳቸውን ከማህበረሰቡ በመነጠል የራሳቸውን ጥቅም ብቻ በማሳደድ ከህዝብ ተነጥለው የኖሩ ናቸው።በዚህም ምክንያት የአማራ ምሁራን በአማራ ህዝብ ዘንድ እንደ ከሃዲና ሆዳም እየተባሉ በየስብሰባውና በየማህበራዊ ሚዲያ ሲጠቀሱ መቆየታቸው የሚታወስ ነው።

አማራ በህወሓት ተቀፍድዶ ለሩብ ክፍለ ዘመን በባርነት ከቆየ በኋላ የአማራ ፋኖና ወጣቱ፣ ጋዜጠኛውና ሌሎችም ባደረጉት ከፍተኛ መሰዋትነት ህወሓት መቀሌ እንዲከትም ተገዷል። የህወሓትን መቀሌ መመሸግ ተከትሎ የሕህዝቡን ትግል በመንጠቅ የብአዴንና የኦዴድ ብልጣብልጥ ፖለቲከኞች ራሳቸውን የለውጡ ሐዋሪያ አድረገው ተቀመጡ።ለተወሰነ ጊዜም ህዝቡን አታለሉ፤ ግን ብዙ አልቆዩም። አትዮጵያ ሱስ ናት ያሉት ሁሉ ሱሳቸው እነደ ጢስ በኖ ጠፋ፤ ህገ-መንግስቱ እንዲሻሻል እንሰራለን፤ የማንነትና የወሰን ችግሮች እንዲፈቱ እናደርጋለን በማለት አዴፓ ለተወሰነ ጊዜ በህዝቡ ። እየዋለ እያደረ ግን አዴፓ በኦዴድ ቁጥጥር ስር ከመዋሉም ባሻገር የኦነጉ አቢይ ተላላኪ በመሆን የአማራን ጀግኖች ቀስ በቀስ ማጥፋት ተያያዘው፤ ለህዝብ የገባውንም ቃል-ኪዳን እረሳው።

የአማራ ህዝብ መዋረድ እጅግ ያንገበገባቸውንና ለህዝባቸው መሰዋት ለመክፈል የቆረጡትን ለምሳሌ ጀነራል አሳምነው ጽጌንና የክልሉን ልዩ ኃይሎች በግፍ አስጨፈጨፈ፤ የተለያዩ ታጋይ ፋኖቸን አንድ ባንድ እያሳደዱ መግደል ስራየ ብለው ቀጠሉ። ለምሳሌ በደቡብ ጎድር ከምከም አካባቢ ፋኖ አስቻለው

ደሴን ከአራት ወራት በፊት ከፌደራል ጋር በማሴር ማስገዳላቸው የሚታወስ ነው። ፋኖ አስቻለው ደሴ ኦነግ በሰሜን ሸዋ ለመፈንጨት ሲሞክር አይቀጡ ቅጣት ገርፈው ካባረሩት የአማራ ፋኖዎች መካከል አንዱ ነበር።

አማራ በሁሉም አቅጣጫ የጦርነት ነጋሪት እየተጎሰመበት እያየ፣ የአቢይ ክልል/ኦሮሞ ክልል ለ30ኛ ጊዜ ልዩ ኃይል ሲያሰመርቅ እየተመለከተች አዴፓ የአማራ ልዩ ኃይል አዛዥ የነበረውን ጀነራል ተፈራ ማሞን እነ አቢይን ለማስደሰት ሲባል ብቻ በማይመጥነውና በማይመለከተው የውሃ ኮንስትራክሽን አማካሪ ሲያደርግ ኮሌነል አለበልን የመንገዶች ሥራ አማካሪ አድርጎ በመመደብ ለአማራ ህዝብ ችግሮች ፍፁም ግድ የማይለው፣ሆድ አምላኩ የሆነ፣ ለነገ ኢትዮጵያ እንኳ የማያስብ የደነታቢሶቸ ስብስብ መሆኑን በተግባር አስመስክሯል። የአማራ ህዝብ የህልውና ትግል የገባቸውን አባላቱን እንዴት እያሸማቀቃቸው እንደሚገኝ ከአቶ ዮሐኒስ ቧያለው መገንዘብ ይቻላል።

አዴፓ በህወሓት የሚደገፈው የቅማንት ኮሚቴ በተደጋጋሚ በጎንደር አካባቢ በፈጠረው አለመረጋጋት ለመቀልበስ የፋኖ ሚና እጅግ ከፍተኛ እንደነበርና አሁንም ፋኖ ከየትኛውም አቅጣጫ ለሚመጣ ጠላት ፈጥኖ ደራሽ ኃይል መሆኑን በሚገባ ይረዳል። ነገር ግን ፋኖ ለህወሓትና ለኦነግ የእግር እሳት ነው። አዴፓ ደግሞ አለቃው ኦነግን ከሚከፋው አማራ ቢጠፋ ምኑም አይደለም።ለዚህም የተናንቱን የህወሓት አሽከር የዛሬው የኦነግ ሎሌ አዴፓ ፋኖን በወንጀለኛነት ፈርጆ በማሳደድና በመግደል ላይ ይገኛል። የፋኖን አከርካሪ ለመስበርም እንደ ስልት የተወሰደው ታዋቂውን የፋኖ መሪ መሳፍንት ተስፋን ለመግደል ዘመቻው በጎንደር ተጀምሯል። በዚህም የአዴፓ መሰሪ ስራ የክልሉ ልዩ ኃይልና ፋኖ በአንድ ላይ ተሰልፈው የጋራ ጠላታቸውን መመከት ሲኖርባቸው እርስ በርስ እንዲገዳደሉ አድርጓል። እጅግ ያሳፍራል፤ ያበሰጫልም።

በፋኖና በተላላኪው አዴፓ ግጭት ምክንያት አንድ ያልተጠበቀና ድብቅ ሆኖ የቆየ ነገር አሁን ግልጽ ሆኖ ወጥቷል፤ እርሱም በቅርብ ጊዜ የተቋቋመው የአማራ ምሁራን ጉባኤ ተብየው የአቋም መግለጫ ነው።

የአማራ ምሁረን ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ከጥቂቶች በስተቅር ራሱን በማድለብ የኖረ፣ የአማራን ህዝብ በማደራጀትና በመምራት ለነፃነት እንዲታገል ከመስራት ይልቅ በራስ ወዳድነት ተጠምዶ የአማራ ህዝብ ለህልውና አደጋ እንዲጋለጥ ካደረጉት ምክንያቶች አንደኛው ነው።

ከአማራ ምሁራን መካከል የአማራ ህዝብ የህልውና አደጋ ውስጥ መግባቱ ቀድሞ የተረዱት ታላቁና የተከበሩት ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ መዐድን ሲመሰርቱ የአማራን በብሄር መደራጀት ከተቃወሙት ጸረ-አማራ ኃይሎች መካከል አንዱ የአማራ ምሁራን ይገኙበታል፤ ይህ ጸረ-አማራ እንቅስቃሴ የእውቁን ሐኪም ፕሮፌሰር አስራትን ህይውት በሚያሳዝን ሁኔታ እንዲያልፍ አድርጓል። የአማራ ምሁራን ተብየዎች ከሃያ አመት በኋላ እንኳ የህዝብ ፍቅር ምን ማለት እንደሆነና ምሁር ማለት ለእውነት መቆም እንደሆነ ከፕሮፌሰር አስራት መማር አልቻሉም፤ምክንያቱም ሆዳቸው ህሌናቸውን ደፍኖታል። የአማራ ምሁራን የህዝባቸው መዋረድ አይደለም የሚያሰጨንቃቸው፤ እነረሱ መዋረድ የሚሉት አማራ በአማራነቱ መደራጀት ነው። አማራ እንደ ህዝብ መኖር ካልቻለ እነርሱና ልጆቻቸው መኖር እንደማይችሉ የተረዱ አይመስልም።

ፋኖ በከፈለው መሰዋትነትና በተገኘው አንፃራዊ የመደራጀት መብት ተጠቅሞ የአማራ ምሁራን ጉባኤ ባለፈው አመት መቋቋሙ ይታወቃል። ጉባኤው ሲመሰረት ብዙዎች እሰየው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ባንዳው አዴፓ ሆን ብሎ ያቋቋመው ነው በሚል ስጋታቸውን ሲገልጹ ቆይተው ነበር። አሁን ግን ግልጽ ሁኗል።

በሰሞኑ በአዴፓና ፋኖ መካከል በተፈጠረው ግጭትና ባስከተለውም የህይወት መሰዋትነት የአማራ ምሁራን ጉባኤ እንደ ፓርቲ የአቢይን ተላላኪ የአቶ ተመስገን ጥሩነህን መግለጫ በአላማ አንድ የሆነ ነገር ግን ለየት ባለ አቀራረብ በማስተጋባት አዴፓነቱን በተግባር አረጋግጧል።አሁን በአማራ ምሁራን ጉባኤ መምታት የለም፤ምክንያቱም ጉባኤው ጭምብሉን አውልቆ በግልጥ እያየነው ስለሆነ። ስሆነም፤ የአማራ ምሁራን ጉባኤ አዴፓ ነው፤አዴፓም የአማራ ምሁራን ጉባኤ ነው።

ይህ የምሁር ተብየ ቡድን ገለልተኛ ቢሆን ኑሮ ቀድሞ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የነበረውን ልዩነት በማጥበብ ወደ አንድ እንዲመጡ ለማድረግ ሲጠር ባየነው ነበር፤ ችግሩ ከተፈጠረም መኋላ ቢሆን መግለጫ ከማውጣት ተቆጥቦ ሁለቱ አካላት ወደ ድርድር እንዲመጡ መስራት ነበረበት፤ ግን ሁለቱንም አላደረገም።

ለመሆኑ የአማራ ምሁራን ጉባኤ 45 ሺህ የአማራ ተማሪዎች ከኦሮሞ ክልል ተባረው ቤት ዋይ ሲሆኑ ምን ተጨባጭ እርምጃ ወሰደ፤ ምን መግለጫስ አወጣ? አስራ ሰባት(17) የአማራ ሴት ተማሪዎች በኦነግ ታግተው መጫወቻ ሲሆኑ ምን ሰራ? በጥቅምት ወር 2012 ዓ.ም ከ86 ሰው በላይ(አብዛኛው አማራ) በኦሮሞ ጽንፈኞች ሲታረዱ ትንፍሽ ያሉት ነገር አለ? ከአራት መቶ በላይ ሰው ቁስለኛ ሲሆን፤ አብዛኛው አማራ ተፈናቅሎ በደብረ ብረሃን ከተማ እንዲሰፈር ሲገደድ ምን መግለጫ አውጣ?

የአማራ ምሁራን ጉባኤ በአዴፓ የድጋፍ መግለጫው እነ መሳፍንት ተስፉንና መሰል ፋኖዎችን እንደሚከተለው ገልጧል '"ሕገ-ወጥ ቡድኖች በትክክለኛ ስማቸው በውንብድና የተሰማሩ ወንጀለኞች ተብለው ሊጠሩ እና ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል" ይላል።

ለመሆኑ የአማራ ምሁራን ተብየው እነ መሳፍንትን ወንበዴ ብሎ ከሰየመ ትክክለኛ ፋኖ የሚላቸው እነማንን ነው? የአማራን ህዝብ ለሩብ ክፍለ ዘመን ሲገድልና ሲያሳድድ በነሮው በህወሓትና ኦነግ ላይ እንዲህ ያለ መግለጫ አውጥቶ ያውቃል?

የተሻለ ለውጥ በክልሉ እንዲመጣ አስተዋጾ ያደርጋሉ ሲባል ጭራሽ የአማራ ህዝብ ዘብ የሆነው ፋኖን ወንጀለኛ በማድረግ እርምጃ እንዲወሰድበት በማድረግ የአማራ ህዝብ በኦነጉ አቢይ ሌላ የባርነት ዘመን እያዘጋጁለት ይገኛሉ። የአማራ ምሁራን ተብየዎች አሁን አንድ ልብ ያላሉት ነገር አለ፤ እርሱም የአማረ ወጣት አንቅሮ የተፋቸው መሆኑንና የወደፊቱ የአማራ ህዝብ ህልውና በአማራ ወጣትና በአማራ ፋኖ የሚወሰን መሆኑ ነው። አዴፓ ከአሁን በኋላ ከአማራ ህዝብ ልቦና ውስጥ ጨርሶ ወጥቷል፤ አዴፓ እያለ አማራ ነጻ ህዝብ እንደማይሆን ተገንዝቧል። ስለሆነም የአማራ ምሁራን ተብየዎች በአማራ ህዝብ ዘንድ የሚኖራችሁን ተቀባይነት በራሳችሁ ቅሌትና አድርባይነት ገድለውታል። የአማራ ምሁራን ተብየዎች እንደለመዱት በህወሓት ዘመን እነደ አይጥ ተደብቀው እንዳሳለፉት ተደብቀው ቢቆዩ ይሻላቸው ነበር።

## ድል ለፋኖ! ፋኖ የአማራ ህዝብ የነፃነት ቀንዲል ነው!